# WIDA የብቃት መለኪያዎች ፍቺ – ማዳመጥ እና ማንበብ ከK-12 ክፍል

## በቋንቋ የመጠቀም ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ

| | የንግግር ልኬት (Discourse Dimension) | የዓረፍተ ነገር ልኬት (Sentence Dimension) | የቃላት/ሃረጎች ልኬት (Word/Phrase Dimension) |
|---|---|---|---|
| | የቋንቋ ውስብስብነት (Linguistic Complexity) | የቋንቋ ቅርፆች እና አገባቦች (Language Forms and Conventions) | የቃላት አጠቃቀም (Vocabulary Usage) |
| **ደረጃ 6- መድረሻ (Reaching)**<br>የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለተለያዩ ትምህርት ተኮር አላማዎችና ታዳሚያን ከክፍል ደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቃል እና የጽሁፍ ቋንቋን ይጠቀማሉ። በትምህርታዊ ቋንቋ ያለ የላቀ ችሎታ በአንደበተ ርቱዕነት እና በፍጥነት ምላሽ በመስጠት እንዲሁም በተለያዩ ርዕሶች ላይ በነጻነት በማውራት እና በግል መስተጋብሮች ላይ ልዩ ክህሎትን በማሳየት ይንጸባረቃል። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ በትምህርታዊ ቋንቋ ላይ ያለው ብቃት በይዘት ዘርፍ ጽንሰ ሃሳቦችን እና ሃሳቦችን የመረዳት ችሎታን ያመቻቻል። | | | |
| በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ላይ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ማብቂያ አካባቢ በመምህሩ ድጋፍ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ... | | | |
| **ደረጃ 5<br>አሸጋጋሪ (Bridging)** | • የበለጸገ ገላጭ ንግግር ከውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ጋር<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ሃሳብን በተደራጀ፣ ለመረዳት በሚቻል እና ፍሰት ባለው መልኩ መግለጽ | • የተለያዩ ውስብስብ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በአንድ የተወሰነ ዘርፍ ላይ የዓረፍተ ነገር አወራረዶች ባህሪያት | • ቴክኒካዊ እና ውስብስብ የይዘት ዘርፍ ቋንቋ<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ትርጉም ያላቸው ቃላትና አገላለጾች |
| **ደረጃ 4<br>ማስፋፊያ (Expanding)** | • የተለያዩ ዓረፍተ ነገር ያላቸው የተያያዙ ሃሳቦች<br>• በአንድ የተወሰነ የይዘት ዘርፍ ላይ ተዛማጅነት ያላቸው ሃሳቦች ባህሪያት | • ውስብስብ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በተወሰኑ የይዘት ዘርፎች ላይ ተገቢ የሆኑ የዓረፍተ ነገር አገባቦች ባህሪያት | • የተወሰኑ እና ቴክኒካዊ የይዘት ዘርፍ ቋንቋዎች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ የተለያዩ ትርጉም ያላቸው ቃላትን እና አገላለጾችን መጠቀም |
| **ደረጃ 3<br>አዳጊ (Developing)** | • ረዘም ያሉ ተከታታይ ዓረፍተ ነገሮች ሃሳብ መግለጽ<br>• አንድን የይዘት ዘርፍ ውስጥ ያሉ ተያያዥ ሃሳቦች | • ሁሉን አቀፍ እና የተወሰኑ ውስብስብ ሰዋሰዋዊ አወቃቀሮች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ውስጥ ያሉ የዓረፍተ ነገር አወራረዶች | • የተወሰኑ የይዘት ዘርፍ ቋንቋዎች እና አገላለጾች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ያሉ የጋራ ተዛማጅነት ያላቸው ቃላት እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች |
| **ደረጃ 2<br>ጀማሪ (Emerging)** | • ከአንድ በላይ ተዛማጅ ዓረፍተ ነገሮች<br>• ዝርዝሮች ያሉት ሃሳብ | • መሰረታዊ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በተለዩዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ተደጋጋሚ የሃረግ እና የዓረፍተ ነገር አወራረዶች | • ተዛማጆችን ጨምሮ አጠቃላይ የይዘት ቃላት እና አገላለጾች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ያሉ ማህበራዊ እና ትምህርት ነክ ቃላትና አገላለጾች |
| **ደረጃ 1<br>መግቢያ (Entering)** | • ነጠላ መግለጫዎች ወይም ጥያቄዎች<br>• በቃላት፣ በሃረጎች ወይም ተያያዥ የሆኑ የቋንቋ ቃላቶች ውስጥ ያለ ሃሳብ | • ቀላል ሰዋሰዋዊ አወቃቀር (ለምሳሌ፣ ትዕዛዞች፣ Wh-ጥያቄዎች፣ ውሳኔዎች)<br>• ከተለመዱ ማህበራዊ እና ትምህርታዊ ሁኔታዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ፎርሞች እና አወራረዶች | • አጠቃላይ ከይዘት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቃላት<br>• የዕለት ተዕለት ማህበራዊ፣ ትምህርት ነክ እና ከይዘት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቃላት እና ሃረጎች |



WIDA™

## WIDA የብቃት መለኪያዎች ፍቺ – መናገር እና መጻፍ ክፍል K-12

### በቋንቋ የመጠቀም ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ

| | የንግግር ልኬት (Discourse Dimension) | የዓረፍተ ነገር ልኬት(Sentence Dimension) | የቃላት/ሃረጎች ልኬት (Word/Phrase Dimension) |
|---|---|---|---|
| | የቋንቋ ውስብስብነት (Linguistic Complexity) | የቋንቋ ቅርፆች እና አገባቦች (Language Forms and Conventions) | የቃላት አጠቃቀም (Vocabulary Usage) |
| **ደረጃ 6- መድረሻ (Reaching)**<br>የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለተለያዩ ትምህርት ተኮር አላማዎችና ታዳሚያን ከክፍል ደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ቋንቋን ይጠቀማሉ። በትምህርታዊ ቋንቋ ያለ የላቀ ችሎታ በአንደበተ ርቱዕነት እና በፍጥነት ምላሽ በመስጠት እንዲሁም በተለያዩ ርዕሶች ላይ በነጻነት በማውራት እና በግል መስተጋብሮች ላይ ልዩ ክህሎትን በማሳየት ይንጸባረቃል። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ በትምህርታዊ ቋንቋ ላይ ያለው ብቃት በእያንዳንዱ የትምህርት ይዘት ዘርፍ ውስጥ መረጃዎችን እና ሃሳቦችን በትክክል እና በተራቀቀ ሁኔታ ለማገናኘት ያላቸውን ችሎታ ያመቻቻል። | | | |
| በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ላይ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ማብቂያ አካባቢ በመምህሩ ድጋፍ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ... | | | |
| **ደረጃ 5**<br>**አሸጋጋሪ (Bridging)** | • ከአንድ በላይ፣ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች<br>• በአንድ የተወሰ የይዘት ዘርፍ ላይ ሃሳብን በተደራጀ፣ ለመረዳት በሚቻል እና ፍሰት ባለው መልኩ መግለጽ | • የተለያዩ ውስብስብ ሰዋሰዋዊ አገባቦችን መተበጊው ቦታ ላይ መጠቀም<br>• በአንድ የተወሰነ ዘርፍ ላይ የተለያዩ አይነት የዓረፍተ ነገር አወራረዶችን | • ቴክኒካዊ እና ውስብስብ የይዘት ዘርፍ ቋንቋን፣ ለይዘቱ ከተወሰኑ ማነጻጸሪዎችን ጨምሮ<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ትርጉም ያላቸው ቃላት እና አገላለጾች |
| **ደረጃ 4**<br>**ማስፋፊያ**<br>**(Expanding)** | • አጭር፣ ረዘም ያሉ እና የተወሰኑ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች<br>• በአንድ የተወሰነ የይዘት ዘርፍ ላይ ፍሰት ያለውና በአግባቡ የተደራጀ የሃሳቦች አገላለጽ | • ሁሉን አቀፍ እና ውስብስብ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በተወሰኑ የይዘት ዘርፎች ላይ ተገቢ የሆኑ የዓረፍተ ነገር አገባቦች | • የተወሰኑ እና ቴክኒካዊ የይዘት ዘርፍ ቋንቋዎች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ንጽጽሮችን እና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም ገላጭ የሆኑ ቃላትን እና አገላለጾችን መጠቀም |
| **ደረጃ 3**<br>**አዳጊ (Developing)** | • አጭር እና የተወሰኑ ረዘም ያሉ ዓረፍተ ነገሮች በመታየት ላይ ያለ ካለ ውስብስብነት ጋር<br>• አንድን ሃሳብ በተስፋፋ ሁኔታ መግለጽ ወይም በተለያዩ የይዘት ዘርፍ ውስጥ ያሉ ከአንድ በላይ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን መግለጽ | • አልፎ አልፎ የሚለያዩ ቀላል እና ሁሉን አቀፍ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ውስጥ ያሉ የዓረፍተ ነገር አወራረዶች | • የተወሰኑ የይዘት ቋንቋዎች፣ ተዛማጅ ቃላትንና አገላለጾችን ጨምሮ<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ያሉ ከአንድ በላይ ትርጉም ያላቸው ቃላትን ወይም አገላለጾች |
| **ደረጃ 2**<br>**ጀማሪ (Emerging)** | • ሃረጎች ወይም አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች<br>• በመታየት ላይ ያለ የሃሳቦች አገላለጽ | • መሰረታዊ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• በተለዩዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ተደጋጋሚ የሃረግና የዓረፍተ ነገር አወራረዶች | • አጠቃላይ የይዘት ቃላት እና አገላለጾች<br>• በተለያዩ የይዘት ዘርፎች ላይ ያሉ ማህበራዊ እና ትምህርት ነክ ቃላትና አገላለጾች |
| **ደረጃ 1**<br>**መግቢያ (Entering)** | • ቃላት፣ ሃረጎች ወይም የተቆራረጡ ንግግሮች<br>• ሃሳቦችን ለመግለጽ ነጠላ ቃላትን መጠቀም | • በሃረግ ደረጃ ያሉ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች<br>• ከተለመዱ ማህበራዊ እና ትምህርታዊ ሁኔታዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሃረግ አወራረዶች | • አጠቃላይ ከይዘት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቃላት<br>• የዕለት ተዕለት ማህበራዊና ትምህርት ነክ ቃላትና አገላለጾች |